Ginbot 7: Movement for Justice Freedom and Democracy
የግንቦት7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

---

ቀን ነሐሴ 26፣ 2001
ቁጥ- 002/08

# የግንቦት7 ድምጽ ሬድዮ ፕሮግራም መስከረም 1፣2001 ዓ.ም ይጀመራል።

በአገራችን ላይ የተንሰራፋው አምባገነናዊ አገዛዝ፣ ግፈኛ ስርአቱን ማራዘም ከሚችልባቸው መሳሪያዎች አንዱ ህዝብ ስለሃገሩ አጠቃላይ ሁኔታ በቂ መረጃ እንዳያገኝ፣ እርስ በርሱ ተገናኝቶ እንዳይመክር፣መክሮም አስከፊ ህይወቱን ለመቀየር በጋራ እንዳይነሳ በማድረግ ነው፡፡ ባለፈው 17 አመታት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሃገሪቱን የመገናኛ ብዙሃን በተለይ ብዙሃኑን በቀላሉ መድረስ የሚችሉትን፣ ራድዮና ቴሌቪዥን በሞኖፖል ይዞ፣ በአፍሪካ ውስጥ እንኳን የሚታየውን የሚድያ ነጻነት የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይጎናጸፍ አፍኖ የያዘበት ምክንያት ህዝብ ከነጻ ሚድያ በሚያገኘው መረጃ ከታጠቀ፣ ለመብቱና ለጥቅሙ እንደሚነሳ በመፍራት ነው፡፡ በእዚህ ታፍኖ ያለተቀናቃኝ በተያዘ ራድዮና ቴሌቪዥን ቀንና ማታ በሬ ወለደ አይነት ውሸቶችን ሲቀድበት፣ ረሃብን ጥጋብ አድርጎ ሲያቀረብበት፣ ድህነትንና የኑሮ ውድነትን ያመጣሁትን የኢኮኖሚ እድገት እዩልኝ ሲልበት፣ ዳር ድንበርን ቆርሶ በመስጠት የአገር ክህደት እየፈጸመ መልካም ጉርብትና እየተከተልኩ ነው ብሎ ሲያላግጥበት፣ ዘረኛ ከፋፋይነትን እያስፋፋ፣ መብት አስከብሬ ያመጣሁት አንድነት እያለ ሲያሾፍበት፣ ራሱ ባጭበረበረው የምርጫ ውጤት ሰበብ ዜጎችን በአረመናዊ ጭካኔ በጠራራ ፀሃይ ገሎ የተጭበረበረውንና የሞተውን ህዝብ መልሶ ሲወነጅልበት አይተናል፡፡

የግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በተወሰደው የአፈና እርምጃ ለተወሰኑ አካባቢዎች በመጠኑም ቢሆን የተለያዩ አስተሣሰቦችን ሲያቀርቡ የነበሩ የግል ፕሬሶች በቀጥታና በተዘዋዋሪ በደረሰባቸው ጥቃት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ሲደረግ፣ ከሁለት ዓመት እስር በሁዋላ ከተፈቱት ጋዜጠኞች መካከል አንዳንዶቹ በወከባ መብዛት አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ተደርገዋል፣ የተቀሩት ከፊሎቹ ጋዜጣ በማሳተም ሥራ ለመሰማራት ጠይቀው ተከልክለዋል፡፡ በብዙ ችግርና መስዋዕትነት በአዲስ መልክ ተደራጅተው ህትመት ለመጀመር የሞከሩ ጥቂት ጋዜጦች ደግሞ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ስጋትና በአደጋ ውስጥ ይገኛሉ። ከዚያም ባሻገር የተለያዩ አስተሣሰቦች የሚንሸራሸሩባቸው ኢትዮጵያዊ ድረ-ገፆች ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይደርሱ ታግደዋል። በራሱ አንጡራ ሃብት ከሚተዳደረው የመገናኛ ብዙሃን እርባና ያለው መረጃ መግኘት የተሳነው ህዝባችን እንደብቸኛ አማራጭ የሚገለገልባቸው የአሜሪካና የጀርመን ድምፅ ሬዲዮኖች ሳይቀሩ ወደ 14 ሚልዮን የሚጠጋው ወገናችን በረሃብ አለንጋ በሚሰቃይበት በአሁኑ ጊዜ ጭምር ከፍተኛ የውጭ ሚንዛሪ እየፈሰሰበት እንዲታፈን ተደርጎአል ;; ይባስ ተብሎ በአዲስ አፋኝና ጨቋኝ ህግ ከለላ፤ በሃገሪቱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ የመብት ጭላንጭል ለአንዴና ለመጨረሻው ለማዳፈን ቆርጦ ተነስቷል፡፡

በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ ነው፣ አምባገነናዊነትን ወደ ታሪክ ትቢያነት ለመለወጥ የተነሳው የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ በሣምንት አንድ ቀን ከሚያዘጋጀው ጋዜጣ በተጨማሪ፤ በአዲሱ ዓመት ነጻነት ለተጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ አዲስ የተስፋ ስጦታ ለማቅረብ ዝግጅቱን ያጠናቀቀው።"መረጃ ሃይል ነው፡፡ በመረጃ የታጠቀ ህዘብ ለመብቱ፣ ለነጻነቱ፣ ለጥቅሙና ለሃገሩ ደህንነት የቆረጠ ታጋይ ይሆናል" ከሚል እምነት በመነሳት፤ ንቅናቄያችን በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም መስከረም 1 ቀን 2001 ዓ.ም ሐሙስ ምሽት ይጀምራል።ፕሮግራሙ ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ በኦሮሚኛና ትግርኛ ቋንቋዎች ስርጭቱን ያቀርባል።በተጨማሪም ፕሮግራሞቹን ከግንቦት 7 ድረ-ገጽ ላይ በመጫን ማዳመጥ የሚቻልበት ሁኔታም መመቻቸቱን እንገልጻለን።

የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ

www.ginbot7.org